# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

**1**

ሚያዝያ ፴-፲፱፻፸፰ ዓ. ም.

★ የኢትዮጵያ መደቦችና አሰላለፋቸው

★ ሌኒን ስለ ድርጅት

★ የጥናት ክበቦች አመሠራረት...

፩ኛ ዓመት
ቍጥር ፩ ።

ዋጋው ሃያ አምስት ሳንቲም ብቻ ።

## ርእሰ አንቀጽ ።

# ጋዜጣና አብዮታዊ ትግል ።

የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከደመኛ ጠላቶቻቸው ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር መራራ ትግል ሲያካሒዱ ብዙ ዘመናት አሳልፈዋል ። ይህ በትግላቸው ከጊዜ ወደጊዜ ያዳበሩት ትግል በየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. አዲስና አኩሪ ምዕራፍ ከከፈተ ወዲህ ፊውዳሊዝምን ለመደምሰስ ፤ ኢምፔሪያሊዝምን ከኢትዮጵያ ምድረ ገጽ ጨርሶ ለማጥፋት የሚደረገው ታሪካዊ ተጋድሎ ወደፊት በመግፋት ላይ ነው ።

በዚህ አዲስ ምዕራፍ በከፈተው ትግል የኢትዮጵያ ጭቁኖች ብዙ ድሎችን ተጐናጽፈዋል ። የገጠር መሬትን ለሕዝብ ፤ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤቶችን ፤ አንዳንድ የማምረቻና የማከፋፈያ መሣሪያዎችን የመንግሥት ያደረጉት አዋጆችን በትግላቸው አግኝተዋል ። ይሁን እንጂ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለማውደም በሚያደርጉት ትግል ገና ብዙ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል ። ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት በሚገኝበት አዋሳኝ መድረክ ላይ እስከአሁን ለተገኙት ድሎች ዋስትና ለመስጠትና ሌሎች ድሎችንም ለመጐናጸፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ በይበልጥ ተደራጅቶና ታጥቆ ትግሉን ማፋፋም ይኖርበታል ። ተራማጆችም ሰፊውን ሕዝብ በማንቃትና በማደራጀት አብዮቱ ከግቡ እንዲደርስ መጣር ታሪክ የጣለባቸው ከፍተኛ ኃላፊነት ነው ።

አብዮታዊ ትግልንም ለማካሔድ ተራማጆችና ሰፊው ሕዝብ ከሚገለገሉባቸው ዋና ዋና መሣሪያዎች አንዱ አብዮታዊ ጋዜጣ ነው ። ጋዜጣ ዓይነተኛ የቅስቀሳ መሣሪያ ስለሆነ ሰፊው ሕዝብ ዕለት በዕለት ከሚደርሱበት ችግሮች እየተነሳ ፤ የነዚህን ችግሮች ምንጭ በማሳየት ፤ ወደተጨባጭ መፍትሔያቸው የሚያመራውን የትግል መንገድ ያብራራለታል ። የሰፊውን ሕዝብ የፖለቲካ ፤ የኤኮኖሚና የሶሻል ትግል በመልክ በመልኩ እየለየ ፤ በተወሰነ ጊዜና ሁኔታ ከነዚህ ሦስት የትግል ዘርፎች አንፃር መቅረብ ያለባቸውን ጥያቄዎች እያመለከተና እያብራራ ትግሉ እንዲቀናበር ያደርጋል ። በተወሰነ ጊዜ ፤ ጠላቶችን እንደ የመልካቸው እያሳየ ፤ ሰፊው ሕዝብ ኃይሉን ሰብስቦ ጠላቶቹን በየደረጃው የሚመታበትን የትግል ስልት ያስተምራል ።

ጋዜጣ ዓይነተኛ የትምህርት መሣሪያ ነው ። ሰፊው ሕዝብ በጭቆና አገዛዝ ከሚደርስበት ስቃይ የተነሣ ያለበትን ሥርዓት ይጠላል ፤ ለትግልም ይነሳሳል ። ግን አንድን ሥርዓት ለመለወጥ ጥላቻና ገንፍሎ መነሣት ብቻ አይበቁም ። ሰፊው ሕዝብ በጠላው ሥርዓት ቦታ ምን ዓይነት ሥርዓት መተካት እንደሚገባውና ለመመሥረትም እንደሚችል ማወቅ አለበት ። አዲስ ሥርዓትን ለመገንባት በየጊዜው የሚታለፍባቸውን የትግል ደረጃዎችና ተስማሚውን የትግል ሥልት ማወቅ አለበት ። ባጭሩ ሰፊው ሕዝብ ያሰቃየው የነበረውን ሥርዓት በመጥላት ብቻ የሚመረር ሳይሆን የወደፊቱንም ሥርዓት ገንቢ አብዮታዊ ኃይል መሆኑን የሚገነዘብ ለማድረግ አንዱ መሣሪያ ተራማጅ ጋዜጣ ነው ።

ስለዚህ በተከታታይ የሚወጣ ተራማጅ ጋዜጣ ፤ በአጠቃላይ ሶሻያሊዝም ምን እንደሆነ ፤ መቼና በምን ሁኔታ በአገራችን ሊገነባ እንደሚችል ፤ በዛሬው ትግልና ሶሺያሊዝምን ለማምጣት በሚደረገው ትግል መሀል ያለውን ዝምድናና ልዩነት በማሳየት የታጋዮችን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት ከፍ ለማድረግ ይችላል ። እንዲሁም በዛሬው የትግል ደረጃ የአብዮቱ መሠረታዊ ጠላቶች ፊውዳሊዝም ፤ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ምን እንደሆኑ ፤ እነርሱን ደምስሶ የሚተካውን

የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ምንነት በማብራራት ፤ ለዚህ አብዮት ስኬት ከፍ ያለ ግልጋሎት ይሰጣል ።

ከዚህም አልፎ ጋዜጣ የጠላት ሠፈርን ሥራና ሴራ ማጋለጫ መሣሪያ ነው ። በዝባዥ መደቦች በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ፤ ድሎታቸውንና ሀብታቸውን አይለቁም ። ይህንን የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ባለፉት ዓመታት ያካሔዳቸው ትግሎች መስክረውለታል ። በአብዮታዊ ትግል ተገፍተው የወደቁ በዝባዦች ተስፋ ቆርጠውና እጃቸውን አጥፈው አይቀመጡም ። እንዲያውም እንደቆሰለች አውሬ ይብልጥ የሚፈራገጡት ከወደቁ በኋላ ነው ። ይህ ዓይነቱ መፈራገጥ መላላጥ ቢሆንም ፤ ስለዚህም ሥልጣን ላይ ለመመለስ ፤ የጭቆና አገዛዛቸውን በተቀየረ መልክ እንደገና በሰፊው ሕዝብ ላይ ለማስፈር ፤ የማይጠነስሱት ሴራ ፤ የማይገለብጡት ድንጋይ አይኖርም ። ተራማጅ ጋዜጣ ይህንን የአድኃሪዎች ሴራ በጊዜው መርምሮ እያጋለጠ ፤ ሴራቸው በሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ኃይል የሚደመሰስበትን መንገድ ያመለክታል ።

ጋዜጣ የጠራ የፖለቲካ መሥመር መንደፊያ ፤ የርእዮተ ዓለም ትግል ማካሔጃ መሣሪያ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች የሚደረገውን ዲሞክራሲያዊ አብዮት ለማካሔድ የሚፎካከሩ ብዙ መደቦችና ክፍሎች አሉ ። የዚህን ንቅናቄ መሪነት ለመያዝ በንዑስ ከበርቴውና በወዛደሩ መደብ መካከል የሞትና የሽረት ትግል ይካሔዳል ። አብዮቱን ከፍጻሜ ማድረስ የሚችለው የወዛደሩ መደብ ብቻ መሆኑ በታሪክ ከተመሰከረ ወዲህ ፤ ብዙ የወዛደሩ መደብ አባል ያልሆኑ ክፍሎች የሚናገሩትና የሚነሡት በወዛደሩ ስም ነው ። የወዛደሩ መደብ የዚህን አብዮት አመራር ለመውሰድ የሚችለው በይገባኛል ሳይሆን ፤ በርሱ ስም ከሚመጻደቁ ክፍሎች ጋር በሚያደርገው ኃይለኛ የርእዮተ ዓለም ትግል አሸናፊነትን ሲያገኝ ብቻ ነው ። ስለዚህም ፤ በተለይ ወገን ለይቶ በወዛደሩ ጐን የተሰለፈ ጋዜጣ ፤ ሳይንሳዊውን የወዛደር ርእዮተ ዓለም ለመበረዝ የሚነሱ ኃይሎችን ፀረ—ሳይንስ አስተሳሰብ እያጋለጠ ፤ በወዛደሩና በሰፊው ሕዝብ መሀል የጠራው ሳይንሳዊ ርእዮተ ዓለም ሥር እንዲሰድ ይታገላል ።

በተጨማሪም ፤ በአጠቃላይ ግምቶች ላይ ፤ በተለይ ከተጨባጩ ሁኔታ የራቁ ሳይንሳዊ ሀቆች ላይ ብዙውን ጊዜ በተለይ በወዛደሩ ስም ከሚመጻደቁ ኃይሎች እነአስፋወሰን/ መንገሻ ሥዩም ርዝራዦች እንኳ « ዲሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ » ትፈልጋላችሁ ቢባሉ አዎ ይላሉ ። ስለዚህ የርእዮተ ዓለም ትግሉ የሚያተኩረውና ማተኮር ያለበትም በአጣዳፊና በዛሬው የትግል ደረጃ ጊዜ በሚነሱ ጥያቄዎች ለይና አብዮቱ ግቡን እንዲመታ ዛሬ መከተል ያለበትን የትግል ታክቲክ በመተለሙ ላይ ነው ። በወዛደሩ ስም የሚመጻደቁት ሆኑ ሌሎች ፀረ—ወዛደሮች ሊጠቁና ሊጋለጡ የሚችሉት ለነዚህ ጥያቄዎች በሚሰጡት መልሶች ነው ። ለነርሱ ፤ የዛሬው ተጨባጭ የሕዝብ ትግል ትክክለኛ መሥመርና ታክቲክ ካልተከተለ ወደ ድል እንደማያመራ ስለሚያውቁ ይህ ትክክለኛ መሥመርና ታክቲክ እንዳይያዝ እስካደረጉ ድረስ ፤ ስለ « ዲሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ » ስለምድራዊት ገነት ኢትዮጵያ ቢያወሩ እንደማይጐዳቸው ይረዳሉ ። ተራማጅ ጋዜጣ በበኩሉ የዛሬው ተጨባጭ የሕዝብ ትግል ትክክለኛ መሥመርና ታክቲክ ላይ ካልተከዘ ወደ ድል ሊያመራ እንደማይችል ጠንቅቆ ስለሚረዳ ፤ የሕዝቡን ትግል ትክክለኛ መሥመርና ታክቲክ ለማስያዝ ፤ የሕዝቡን ትግል አቅጣጫ ለማሳት ከሚነሱ ኃይሎች ጋር ሁሉ የርእዮተ ዓለም ትግል አካሂዶ ጉጂነታቸውን ማጋለጥ ይኖርበታል ።

ጋዜጣ ታጋዩን ሕዝብ ለማስተባበርና ለማዋሐድ የሚረዳ መሣሪያ ነው ። በዚህም አንጻር ይህ ተራማጅ ጋዜጣ ብሔር—አቀፍ እንደመሆኑ በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩ ወዛደሮችና ሠርቶ አደሮች በጠቅላላው ያሉባቸውን ችግሮች ፤ ያካሔዷቸውን ትግሎች እየተነተነ መላው ሰፊ ሕዝብ ከርሱ

ርቀው የሚገኙት ወገኖቹ የሚያደርጉትን እንዲያውቅና የመደብ ትግሉ በብሔር— አቀፍ ደረጃ የሚ ገኝበትን ሁኔታ እንዲረዳ ያግዛል ። በሌላም በኩል በተለያየ አካባቢ የሚኖረው ሠርቶ አደር የሚ ያካሔደው ትግል እንዲጣመርና እንዲደጋገፍ ይታገላል ።

እንዲሁም ተራማጅ ጋዜጣ ፤ የቅስቀሳ ፤ የመማሪያ ፤ የአድኃሪዎች ሴራ ማጋለጫ ፤ የፖለቲካ ንቃት ማዳበሪያ ፤ የርእዮተ ዓለም ትግል መካሔጃ መሣሪያ ከመሆን አልፎ ሰፊውን ሕዝብ ለትግል የሚያደራጅ ነው ። ሌኒን « የጋዜጣ ሚና አሳብ በማሠራጨት ፤ የፖለቲካ ትምህርት በመስጠትና አጋሾር በመሰብሰብ ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ጋዜጣ አጠቃላይ ፕሮፓጋንዳ አሠራጭ ፤ አጠቃላይ ቀስቃሽ ብቻ ሳይሆን ፤ አጠቃላይ አደራጅም ጭምር ነው » ይላል ። ጋዜጣ ፤ አጠቃላይ አደራጅ ነው ሲባል ብዙ ትርጉም አለው ። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ጥራት ያለው መሥመር ይዞ በመታገ ልና በዚያ መሥመር አካባቢ ታጋዮችና ደጋፊዎች እንዲሰበሰቡ ያደርጋል ። ሁለተኛ ደግሞ በዚህ ጋዜጣ አካባቢ ተሰብስበው ዜና በማቀበል ፤ አሳብ በመስጠትና በመጻፍ እንዲሁም ጋዜጣውን በየ ጊዜው በየቦታው በማዳረስ ፤ በያዛቸው ጽሑፎች ላይ በየአካባቢው ውይይት እንዲከፈት በማድረግ የሚተባበሩ ኃይሎች ሁሉ ለመደራጀት የመጀመሪያውን ርምጃ ወሰዱ ማለት ነው ።

« አብዮታዊት ኢትዮጵያ » በይበልጥ የምታተኩረው በሁለተኛው ተራ ቊጥር በተጠቀሰው በማስተማሩ ላይ ነው ። የዚች ጋዜጣ ዋና ዓላማ የሳይንቲፊክ ሶሻሊዝምን መሠረታዊ አሳቦች በአ ጭር ጊዜ ውስጥ በሀገራችን ለማስፋፋት መሞከር ይሆናል ። ከሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ቲወሪ አንጻርና ከሌሎች ሕዝቦች አብዮታዊ ትግል ትምህርት አንጻር ለኢትዮጵያ አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ትሞክራለች ።

የጊዜው መሠረታዊ ጥያቄና ገና ለረዥም ጊዜ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮት ዓቢይ ጥያቄ ለሚሆነው የመደራጀት ጉዳይ አንድ ቋሚ ዓምድ ይኖራታል ። ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ስለድረጅት ምን አቋም አለው ? የወዝአደሩ ፓርቲ ምንድን ነው ? እንዴትስ ይመሠረታል ? እንዴትስ ይታ ገላል ? ሌሎች የወዝአደር ፓርቲዎች እንዴት ተደራጁ ? በኢትዮጵያ የወዝአደሩና የሌሎች ጭቁን መደቦች በመደራጀቱ ተግባር የሚያደርጉት ትግል የቱን ያህል ገፍቷል ? ምን ችግሮች አሉ ? እንዴትስ እንወጣቸው ? እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች የሚተችበት አንድ ቋሚ የድርጅት ጉዳይ ዓምድ ይኖራታል ።

በተጨማሪ በየጊዜው የተነሡና ሊነሱ የሚችሉ ሌሎች የአብዮቱ ጥያቄዎች አሉ ። የመሬ ጠቅ ጉዳይና የኢትዮጵያ አብዮት ፤ የብሔረሰቦች ጉዳይ ፤ የሴቶች ጭቆና ፤ የኅብረት ግንባር . . . እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ከሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሠረታዊ አሳቦች አንፃር ሊተችባቸው የሚ ገቡ ጥያቄዎች ናቸው ።

ሶሻሊስት አብዮትን ባካሔዱ አገሮች የድል ዋስትና ሊገኝ የተቻለው ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የሚጠይቀውን ሁሉ ለማሟላት በመቻሉ ነው ። በሀገራችን የሶሻሊዝም መሠረተ አሳብ በመስፋፋት ላይ ነው። ነገር ግን ሳይንሱ የሚጠይቀውን በማሟላቱ ረገድ በዚህ በኩል የሚደረገው ጥረት በይበልጥ መፋፋምና በይበልጥ የተቀነባበረ መልክ መያዝ አለበት ። የሶሻሊዝምን ዋና ዋና አሳቦች ለመማርና ለማስተማር የሚረዱ የጥናት ክበቦች በሀገራችን በየቦታው መመሥረት አለባቸው ። « አብዮታዊት ኢትዮጵያ » ጋዜጣ ለነዚህ ጥናት ክበቦች መንደርደሪያ የሚሆኑ የተቀነባበሩ ጥናቶችን በየቊጥሩ ታቀ ርባለች ። በዚህ በመጀመሪያው ቊጥር በሚቀርበው አሳብ ማሠረት በያለበት የጥናት ክበቦች ቢቋ ቋሙ ከሚቀጥለው ቊጥር ጀምሮ በየአሥራ አምስት ቀኑ የሚቀርቡትን የጥናት ርእሶች መከታተል

ይችላሉ ። በመጀመሪያ ደረጃ « ሌኒንዝም » በሚል ርእስ ተቀነባበረው የተዘጋጁ ሠላሳ ትም ህርቶች ይኖራሉ ። በሁለተኛ ደረጃ « ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ » በሚል ርእስ ስር በሐያ አምስት ትም ህርቶች የተከፈለ ፕሮግራም ይቀርባል ። ይህ የጥናት ፕሮግራም ሌሎች ማርክሳዊ ፓርቲዎች ሶሻ ሊዝምን ለማስፋፋት በተጠቀሙበት ፕሮግራም ቅደም ተከተል ላይ የተመረኮዘ ቢሆንም ለሀገራችን ሁኔታ እንዲስማማ ተደርጐ ይቀርባል ።

« አብዮታዊት ኢትዮጵያ » ከአንድ አቅጣጫ ብቻ አሳብ ለማጐረፍ የምትወጣ ጋዜጣ አት ሆንም ። « በአብዮታዊት ኢትዮጵያ » ላይ በሚወጡ ጽሑፎች ላይ ወይም በሌሎች መጽሔቶችና ጋዜ ጦች ላይ ስለወጡ ጽሑፎች ሂስ ለመቀበል አንድ « የሂስ መድረክ » ይኖራታል ። አንባቢዎች በዚህ ዓምድ በመጠቀም አሳባቸውን መግለጥ ይችላሉ ። በተጨማሪም ከአንባቢዎች አጫጭር መልእክ ቶች ፤ አስተያየቶች ፤ አብዮታዊ ግጥሞች . . . ለመቀበል እንዲቻል አንድ የአንባቢዎች ዓምድ ይኖ ራታል ።

« አብዮታዊት ኢትዮጵያ » ለጊዜው ከርእሰ አንቀጹ ሌላ በቋሚነት የሚኖርዋት ዓምዶች ከላይ የተጠቁሱት ናቸው ። ጋዜጠዋ ዋና ዓላማዬ ብላ የያዘችውን ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን የማስፋፋት ተግባር እንድትገፋበት አንባቢዎች በሃሳብም በዘዴም ቢረዷት እያደገችና እየተሻሻለች ትሄዳለች ።

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።